የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ሦስተኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጀ መምሪያ
የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ


የቤተክርስቲያን ታሪክ
ሦስተኛ ክፍል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ 2015 ዓ.ም

ያግኙን

Email
office@eotc-gssu.org
YouTube
https://www.youtube.com/channel/UC83LE1vp0FBsV2TEfcpSmUg
Facebook
http://facebook.com/EOTC.GSSU
Telegram
https://t.me/EOTCNSSU
Website
https://eotc-gssu.org/a/

Copyright ©
2015 E.C



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት



ብፁዕ አቡነ አብርሃም
የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና
ሥራ አስኪያጅ እና የባህርዳር
ሁገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

ብፁዕ አቡነ ቀለሜንጦስ
በሰንበት ትምህርት ቤቶች
ማደራጃ መምርያ የበላይ
ሊቀጳጳስና የሰሜን ሸዋ ሀገረ
ስብከት ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ
ሲኖዶስ አባል



ማውጫ

ምዕራፍ አንድ
ገነት..... ፫

ምዕራፍ ሁለት
ደብረ ሲና..... ፮

ምዕራፍ ሦስት
ደብረ ታቦር..... ፲፩

ምዕራፍ አራት
ሠርግ ቤት..... ፲፭

ምዕራፍ አምስት
ደብር ቅዱስ..... ፲፱

ምዕራፍ ስድስት
ማህፀነ ዮርዳኖስ ..... ፳፫

ምዕራፍ ሰባት
መንግስተ ሰማያት ..... ፳፯

ዋቤ መጻሕፍት

ለመምህራን ማስታወሻ

በዚህ የሦስተኛ ክፍል የቅዱሳት መጻሕፍት ማስተማሪያ መጽሐፍ የሰፈሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ለማስተማር መምህሩን ሊያግዙ የሚችሉ መመሪያዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል። መምህሩ የማያውቃቸው አዲስ ነገሮች ሆነው ሳይሆን ለማስተማር ወደ ተማሪዎች ከመሄዱ በፊት እንዲዘጋጅባቸው አጽንኦት ለመስጠት ነው። እነዚህ ነጥቦች በቤታቸው ሆነው ልጆቻቸውን ለሚያግዙ ወላጆችም እንደመመሪያነት ሊያገለግሉ ይችላሉ።

• ታሪኩን ከማስተማርዎ በፊት በሚገባ ይረዱት - መምህራን በተቻለ መጠን በዕለቱ ከሚሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና ትምህርቶች ጋር በሚገባ መለማመድ አለባቸው። ይህ ቅድመ ዝግጅት የሚያስተምሩበትን የማስተማሪያ ዘዴ እንዲመርጡ ፤ አስፈላጊውን የመርጃ መሳሪያ እና ከትምህቱ ጋር የሚሔዱ መዝሙሮችን መርጦ እንዲዘጋጁ ከማስቻሉም ባሻገር መምህራን ትምህርቱን ከተማሪዎቹ ህይወትና ካሉበት ነባራዊ ህይወት ጋር ለማዛመድ ይረዳቸዋል።

• ያቅዱ ይተግብሩ - ትምህርት አንዱ ባህርዩ በዕቅድ የሚመራ መሆኑ ነው። ስለዚህ በእያንዳንዱ የትምህርት ዕለት አቅደው ይዘጋጁ።

• የተለያዩ የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎችን ይጠቀሙ፡ ለመማር ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት የሚመጡ ተማሪዎች ሁሉ በተመሳሳይ መልኩ ትምህርት ይረዳሉ ማለት አይቻልም። አንዳንዱ ከመምህሩ የሰማውን የመያዝ ችሎታ ሲኖረው አንዳንድ ተማሪዎች ደግሞ ከምንባብ ይማራሉ። አንዳንዱ የተማረውን በአንዴ ሲይዝ አንዳንዶቹ ደግሞ በተደጋጋሚ ሲተረክላቸው ወይም ሲነገራቸው ይይዛሉ። ስለዚህ መምህራን ይህንን ልዩነት ከግምት በማስገባት የተለያዩ ሥልቶችን መጠቀማቸው ልፋትና ድካማቸውን የሚደግፍ ስለሆነ የተለያዩ የማስተማሪያ ስነ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ እናበረታታለን።

• መልመጃዎችንና የተለያዩ የምዘና ሥልቶችን ይጠቀሙ፡ ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲያስታውሱት በመጽሐፉ የሚገኙትንና ተጨማሪ መልመጃዎችን እና/ ወይም የመማሩን ሂደት የሚደግፉና ታሪኩን እንደገና የምንከልስበት ሁኔታ መጠቀም እንደሚያስፈልግ እንመክራለን።

• በተቻለ መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀሙ፡ መርጃ መሳሪያ የምንላቸው ከሥዕላት ጀምሮ በዙሪያችን ያሉ ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱት መምህሩም ትምህርቱን በቀላሉ ለመሥጠት የሚያግዙት ግብዓቶች ናቸው። በአንዳንድ ጥቂት አጋጣሚዎች የሚታዩ መርጃ መሣሪያዎችን ለማግኘት በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ታሪክን ለማስረዳት በሥዕሎች ወይም በነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ ይጠቅማል።

• ይመዝኑ፡ ከእያንዳንዱ ዓቢይ ርዕስ ቀጥሎ የምዕራፉ ንዑስ ዓላማዎች ተዘርዝረዋል። የእነዚህ ዓላማዎች አስፈላጊነት መምህሩ ምዕራፉን ወይም ንዑስ ምራፉን አስተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ልጆቹ በትክክል ዓላማውን ማሳካታቸውን ለመመዘን እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ ተማሪዎች ዓላማውን ማሳካታቸውን ይመዝኑ። ያልተሳካ ከመሰለዎት ደግሞ የተለያየ ዘዴ ተጠቅመው ለማሳካት እንዲሰሩ እናሳስባለን።

ምዕራፍ አንድ

ገነት

የምዕራፉ ዓላማ

በዚህ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ይህን ትምህርት ተምረው እንደጨረሱ፦

፩ ስለ ገነት ይረዳሉ።
፪ በገነት ውስጥ አዳም በምን አይነት ሁኔታ እንደሚኖር ያውቃሉ።

ገነት

እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት መካከል አንዱ ዓለመ መሬት ነው። በዚህም ስር ከተገኘው ፍጥረት መካከል አንዱ ገነት ነው። ይህም በምስራቅ በኩል የተተከለ እጅግ የተዋበ ሥፍራ ነው።

ይህም ሦስት በር ሲኖረው የምድር ገዢ የሆነው አዳም የሚገባበት እንዲሁም አጋሩ ሄዋን የምትገባበት ሲሆን ሌሌላኛው ደግሞ የሰማይና የምድር የፍጥረት ንጉሥ የሆነው አምላከ አማልዕክት እግዚአብሔር የሚገባበት ነው።

በገነትም እፀ ሕይወት፣ እፀ በለስ እና ሌሎች እፆች ሲገኙ ጊዮን፣ ኤፌሶን፣ ጤግሮስና ኤፍራጥስ የሚባሉት አፍላጋትን የያዘ ነው። አዳም በዚህ ኤደን ገነት ዘወትር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመሆን ለፈጣሪው ለእግዚአብሔር ምስጋና ያቀርብ ነበር።

በዚም እግዚአብሔር በአዳም ምስጋና እጅግ ደስ ይሰኝ ነበር። ስለዚህ ዘወትር በሰርክ ይጎበኘዋል። አዳምም በገነት ኑሮው አትክልት፣ እጸዋት አዝርእት እየተንከባከበ እንስሳት አእዋፋትን እየባረከ ምድርን በተሰጠው ኃላፊነት ባአግባቡ ያስተዳድር ነበር።

እንዲሁ አጋሩ ሄዋን በነገሩ ሁሉ ትረዳው ነበር። ሁለቱም በጸጋ ላይ ጸጋ እየተጨመረላቸው ይሄዱ ነበር። ስለዚህ ከቅዱሳን መላእክት ጋር ፊት ለፊት ይተያዩ ነበር። ዘፍ.፪፥፲-፲፭



መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ

፩ ገነት በየት አቅጣጫ ተተክላ ትገኛለች?

፪ በገነት ያሉት እጽች እነማ ናቸው?

፫ ገነት ስንት በር ወይም መግቢያ አላት እነማንስ ይገቡበታል?

ምዕራፍ ሁለት

ደብረ ሲና

የምዕራፉ ዓላማ

ይህን ትምህርት ተምረው ሲጨርሱ

፩ ስለ ደብረ ሲና ይረዳሉ።

፪ በደብረ ሲና የተሠሩ ሥራዎችን ያውቃሉ።


ደብረ ሲና

ደብረ ሲና በምድያም ሀገር የሚገኝ ተራራማ ሥፍራ ነው። ይህ ተራራ ታሪካዊ ከሆኑ ተራራዎች መካከል አንዱ ነው፣ በዚህ መሠረት ታሪክ ከተፈፅመባቸው ተራራዎች አንዱ ነው ማለታችን ህዝበ እስራኤል ከግብፅ ባርነት በሊቀ ነብያት ሙሴ መሪነት ባህረ-ኤርትራን አሻግሮ በደብረ ሲና ተራራ ሥር ሰበሰባቸው። ህዝበ-እስራአልም እንደመደባቸው ተሰበሰቡ።

ሊቀ ነበያት ሙሴ የቃል ኪዳኑን ታቦት ከእግዚአብሔር ለመቀበል ወደ ተራራው በወጣ ጊዜ የነዌ ልጅ እያሱ ከእግረ ተራራው ሥር ቆየ ሊቀ ነብያት ሙሴ ግን ወደ ተራራው ጫፍ ወጣ በዚያም አርባ ቀን ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር ቆየ እግዚአብሔርም ለሙሴ አስርቱ ትዕዛዛት የተፃፈበትን የቃል ኪዳኑን ታቦት ሰጠው።

እግዚአብሔርም በቃል ኪዳኑ ታቦት እየተገለጸ ይመክራቸውና ይገስፃቸው ነበር ዘወትርም በደመና አምሳል ከሙሴ ጋር ሲነጋገር ይታየያቸው ነበር።

ይህች ተራራ ሦስት ክፍሎች ነበራት ሙሴና እግዚአብሔር የተነጋገሩበት እንዲሁም ኢያሱ በተስፋ ሆኖ ሲጠባበቅበት የነበረና ህዝበ እስራኤል የሰፈሩበት ሦስተኛ ክፍል ነው፡
፡



መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ

፩ ደብረ ሲና የት ትገኛለች?

፪ በግሪ ደብረ ሲና የነበረው የሙሴ አጋር ማን ነው?

፫ ደብረ ሲና ስንት ክፍሎች ነበሯት?

፬ ሙሴ ከእግዚአብሔር ተቀበለው የቃል ኪዳኑ ታቦት ስንት ሕግጋት ነበሩት?

ምዕራፍ ሦስት

ደብረ-ታቦር

የምዕራፉ ዓላማ

ይህን ትምህርት ተምረው ሲጨርሱ

- ስለ ደብረ ታቦር ይረዳሉ።
- በደብረ ታቦር ተራራ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለፈጸመው ታሪክ ያውቃሉ።

ደብረ-ታቦር

ደብረ-ታቦር ማለት የታቦር ተራራ ማለት ነው ይህ ተራራ የሚገኘው በእስራኤል ሀገር ነው። ከጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አበይት በዓላት መካከል አንዱ ነው።

በዚህ ተራራ ላይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስቱን ሐዋርያት ወደ ተራራው ጫፍ ይዞ ሲወጣ ዘጠኙን ሐዋርያት ደግሞ በእግረ ደብር ሥር አኖራቸው።

በዚያም በተራራው ላይ ሙሴ ከመቃብር፣ ነብዩ ኤልያስ ከብሄረ-ሕያዋን መጥተው ስለ ክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ከመሰከሩ በኋላ ሊቀ ነብያት ሙሴ ወደ መቃብሩ፣ ነብዩ ኤልስም ወደ ብሔረ ሕያዋን ተመለሱ ያን ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለው፦ ‹‹በዚህ ሥፍራ ሦስት ዳስ እንስራ አንዱን ለሙሴ መና አውርዶ ባህር ከፍሎ ሰለሚያበላንና ስለሚያሻግረን አንዱን ለኤልያስ ከሰማይ እሳት እያወረደ ጠላታችንን ያጠፋልና አንዱን ላንተ ብንታመም የምትፈውሰን መድኃኒታችን ማስተዋል ጥበብ እንዲኖረን የምታስተምረን ሁሉ እንዲገዛልን ምታደርግልን ›› በማለት እየተናገረው ሳለ ብሩህ ደመና መጥታ ከደነቻቸው።

ከደመናውም ‹‹የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙ›› የሚል ቃል መጣ ሐዋርያቱም ፈርተው ደንግጠው ወደቁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቦ አነሳቸው ለጴጥሮስ ለዮሐንስና ለያዕቆብ በእግረ ደብር ላሉት ሚስጢሩ ሲገለፅላቸው ለእረኞች ደግሞ ጨለማው ተገልጦ ብርሃን ሆኖላቸው ለሊቱን ከብቶቻቸውን ሲጠብቁ በማደራቸው ቤተሰቦቻቸው ሙልሙልና ችቦ ይዘው በመምጣት የሚስጢሩ ተጋሪ መሆን ችለዋል።

ይህም ተራራ ባለ ሦስት ደብር ነበረ፣ የመጀመሪያውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለቱን ነብያት እና ሦስቱን ሐዋርያት የያዘ ሲሆን ሁለተኛው ዘጠኙን ሐዋርት ያካተተ ነው። ሦስተኛው እረኞቹን እና ቤተሰቦቻቸውን የያዘ ስፍራ ነው። ማቴ ፲፯፥፩-፮



መልመጃ ሦስት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ

፩ ደብረ ታቦር የት ይገኛል?

፪ ደብረ ታቦር በኢትዮጵያ በየትኛው ክፍለ ሀገር ይገኛል?

፫ በደብረ ታቦር መጀመሪያ ክፍል ላይ የተገኙ ሐዋርያት እነማን ናቸው?

፬ ከእግረ ደብር የነበሩት ሐዋርያት ስንት ናቸው?

፭ በዚህ ሦስት ዳስ እንስራ ያለው ቅዱስ ጴጥሮስ ለእነማን ነው?

ምዕራፍ አራት

ሠርግ ቤት

የምዕራፉ ዓላማ

ይህን ትምህርት ተምረው ሲጨርሱ

- ስለ ሠርግ ቤት ይረዳሉ።
- ኢየሱስ ክርስቶስ በሠርግ ቤት መስሉ ስላስተማረው ትምህርት ያውቃሉ።

ሠርግ ቤት

በአንድ ሀገር ላይ የነገሠ ንጉሥ ነበር ንጉሡም ታላቅ ድግስ አዘጋጀ ፣በድግሱም ላይ የሚታደሙትን ይጠሩ ዘንድ መልእክተኞችን ላከ፡፡ ለድግሱ የሚያስፈልጉ ምግቡ መጠጡ መስተናገጃ ቦታ መቀመጫ በየመልኩ አዘጋጀ መልእክተኞችም ወደ ነጋዲያን፣ ወደ ገበሪዎችና ወደ ሊሎችም ሄዱ፡፡

ወደ ነጋዲያን በሄዱ ጊዜ ንጉሥ ታላቅ ድግስ አዘጋጅቶ በክብር ጠርቶአችኋል አሏቸው ነጋዲያኑም ንጉሥ በጠራው ድግስ ላይ በፍፁም መገኘት አንችልም ከሥራችን አታደናቅፉን ከዚህ ሂዱልን ብለው አባረሯቸው::

መልዕክተኞችም በመቀጠል ወደ ገበሬዎች ዘንድ ሄዱ ንጉሣችሁ እርሻና ዘር የሚሰጣችሁ ታላቅ የሆነ ድግስ አዘጋጂቶ በክብር ጠርቷችኋል አሏቸው ገበሬዎችም እኛ እርሻ ስላለብን መገኘት አንችልም ብላችሁ ንገሩ ብለው ሰደዷቸው መልዕክተኞችም የተባሉትን ለንጉሡ ነገሩ ንጉሡም እጂግ አዝኖ በሉ ወደ መንገድ ውጡ ያገኛችሁትን ሰብስባችሁ አምጡ ብሎ አዘዛቸው፣ መልዕክተኞችም በመንገድ ያገኙትን ሁሉ ጠሯቸው፣ ተጠሪዎችም ሁሉ ለድግሱ በሚገባ መልኩ ተዘጋጅተው ተገኙ ንጉሡም በድግሱ ላይ የተገኙትን በደስታ ሆኖ ጎበኛቸው ከታደሙት መካከል አንዱ የሰርግ ልብስ ሳይለብስ ተገኘ ያን ጊዜ ንጉሡ ቀርቦ ወዳጄ ሆይ የሰርግ ልብስ ሳትለብስ ለምን በዚህ ታደምክ አለው መልእክተኞችን ጠርቶ ወደ እሳቱ ወስዳችሁ ጣሉት ብሎ አዘዛቸው፡፡ ማቴ ፳፪፥፩-፲፩



መልመጃ አራት

ለሚከተለት ጥያቄዎች መልስ ስጡ

፩ ንጉሥ ታላቅ ድግስ አዘጋጅቶ በመጀመሪያ የጠራው እነማንን ነው?

፪ በሰርጉ ከታደሙት መካከል የሰርግ ልብስ ያለበሰው ታዳሚ ምን ተፈረደበት?

፫ ወደ ሰርግ ቤት ሲኼድ ምን ይደረጋል?

ምዕራፍ አምስት

ደብረ ቅዱስ

የምዕራፉ ዓላማ

ይህን ትምህርት ተምረው ሲጨርሱ

- ስለ ደብር ቅዱስ ይረዳሉ።
- በደብር ቅዱስ ውስጥ ስለተከናወነ ታሪክ ያውቃሉ።

ደብረ ቅዱስ

አዳም ከገነት ከወጣ በኋላ ከኋላ ልጆችን ወለደ። ከወለዳቸውም ልጆች መካከል አንደኛው ቃኤል ሲኖን ሌላው አቤል ይባላል። ቃኤልም በቅናት መንፈስ ሆኖ ወንድሙን አቤልን ገደለው። በዚህም አዳም አና ሄዋን እጅግ አዘኑ።

እግዚአብሔርም የልባቸውን ሐዘን ተመልክቶ በአቤል ምትክ ሴት የተባለ ልጅ ሰጣቸው ሴትም በእናት በአባቱ እና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ተባረከ ነው። በዚህም የተነሳ በገነት አንፃር በነበረው በደብረ ቅዱስ ይኖር ነበር። ደብረ ቅዱስም ለመኖሪያ የተመቸ ሥፍራ ነው።

ሴትም ለመስዋዕት የሚሆን ቦታ በመለየት ልጁ ሄኖስን ጨምሮ ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት የእለት መስዋዕት እየሰዋ ይኖር ነበር። ሄኖስ እና ልጆቹ ይህኑ የአባታቸውን ፈለግ በመከተል እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘት በህይወት ዘመናቸው ሁሉ ኖሩ። በዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር መላዕክት ለመባል በቁ። መጽሐፈ ሄኖክ ም.፪

መልመጃ አምስት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ

፩ ደብረ ቅዱስ የት ይገኛል?

፪ የእግዚአብሔር መላዕክት የተባሉት እነማን ናቸው?

፫ ሴት ማለት ምን ማለት ነው?

ምዕራፍ ስድስት

ማህፀነ ዮርዳኖስ

የምዕራፉ ዓላማ

ይህን ትምህርት ተምረው ሲጨርሱ

- ስለ ዮርዳኖስ ባህር ይረዳሉ።
- በዮርዳኖስ ባህር ላይ ስለተከናወነው ታሪክ ያውቃሉ።

ማህፀነ ዮርዳኖስ

ዮርዳኖስ ዮርና ዳኖስ ከተባሉ ሁለት ወንዞች የተመሠረተ ታላቅ ባሕር ነው። ይህ ባህር የሚገኘው በእስራኤል ምድር ነው በዚህም ምድር ብዙ ታሪካዊ ክንውኖች ተከናውነውበታል። ከነዚህ መካከል አንዱ ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ አዳምና ሔዋንን ከገነት ካባረራቸው በኋላ አዳም አገልጋይነቱ ለሰይጣን ሔዋን አገልጋይነቷ ለሰይጣን የሚል ሁለት የእዳ ደብዳቤ አዘጋጀና አንዱን በዮርዳኖስ ባሕር አንዱን በሲል ጣለው። ስለዚህ አዳምና ሄዋንና ልጆቹ በዲያብሎስ ቀኝ ግዛት ሲገዙ ቆዩ ታድያ የአዳምና ሔዋንን መከራ የተመለከተ እግዚአብሔር ከሰማየሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከስጋዋ ስጋ ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወሰወኖ ከተወለደና በዚህ ምድር ለሠላሳ ዓመት ከተመላለሰ በኋላ በእለተ ማክሰኞ በእኩለ ለሊት መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በሚያጠምቅበት ወደ ዮርዳኖስ ጉዞ ጀመረ።

ዮርዳኖስ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ‹‹ንስሐ ግቡ መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና እያለ›› የሚያስተምርባት ቦታ ነች። በዚህች ቦታ ላይ ያስተምርበታል ንስሐ የሚገቡትን ደግሞ ቀኖና ሰጥቶ ከዛም በኋላ ያጠምቅበታል አጥምቆ ወደ ንስሐ ወደ ቅድስና ህይወታቸው ይመልስበታል። ስለዚህ እያንዳንዳቸው የቅዱስ ዮሐንስን ትምህርት ለመስማት እንዲሁም ደገሞ ከኃጢአታቸው ለመንጻት ሲሉ በዮርዳኖስ ባሕር ዙርያ ላይ ድንኳናቸውን ደኩነው ቃሉን እየሰሙ ጥምቀቱን እየተጠመቁ ይኖሩ ነበረ። ታድያ በዚህ መካከል የክብር ባለቤት መድኃኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዮርዳኖስ ጥር አስር ለጥር አስራ አንድ አጥቢያ መጣ ሰዓቱም ለሊት ስለነበረ በዛ ሰዓት ርግብም በማይኖርበት አዕዋፋት ባረፉበት ሰዓት ወደ ዮሐንስ መጥቶ ‹‹በል ጽድቅን እንፈጽም ዘንድ ትህትናንም እንሠራ አንድ እነሆ አጥምቀኝ›› አለው። መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስም አምላኩን ‹‹ጌታዮ ሆይ አንተኮ ልታጠምቀኝ ይገባል እንጂ እኔ ላጠምቅህ አይገባም›› አለው። ኢየሱስም ‹‹እሺ በልና የትህትናን ሥራ እንስራ ስለዚህ አጥምቀኝ›› አለው አዘዘውም። ‹‹ታድያ ምን ብዮ ነው የማጠምቅህ›› ቢለው ‹‹አብ ቅዱስ ወልድ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ብለህ አጥምቀኝ አለው ያን ግዜም ዮሐንስም እንዳለው አጠመቀው። ዮርዳኖስም ሸሸች ደነገጠችም ፈራች በዮርዳኖስ የነበረውም የሰው ልጆች የእዳ ደብዳቤ ተፋቀ ነጻም ወጡ። ስለዚህ አዳም የዲያቢሎስ ባርያ መሆኑ ቀርቶ የእግዚአብሔር ባርያ ሊሆን እዳው ተሰረዘለት ማለት ነው። ይሄ እዳ በዚህ ቢቆይና ባይሰረዝ ኖሮ የኋላ የኋላ ጠላት ዲያቢሎስ ‹‹አዳምና ልጆቹ እኮ የኔ ናቸው›› በማለት በእግዚአብሔር ፊት ያቀርበው የነበረው እዳ ደብዳቤ ይኖረው ነበር ያም እንዳይኖረው መድኃኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱ የእዳ ደብዳቤውን ሰረዘለት።

በዚህም ዮርዳኖስ የቅድስት ቤተክርስቲያን ምሳሌ ነች። ቅድስተ ቅዱሳን መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተገናኙባት እንዲሁም ደግሞ በቅድስቱ የታደሙት ድንኳናቸውን ደኩነው ቃሉን ሲሰሙ ከጥምቀቱ ሲሳተፉ ንስሐ ሲገቡ የነበሩ እንዲሁም ደግሞ ወደ ዮሐንስ በመምጣት ንስሐ የሚገቡት ደግሞ የምዕመናን ምሳሌ በመሆን የቤተክርስቲያን ምሳሌነቷን አስተምረዋል። ማቴ ፫፥፲፫-፲፯፣ ሉቃ ፫፣ ማርኛ



መልመጃ ስድስት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ

፩ ዮርዳኖስ የተባለው ባሕር የምንና የምን ወንዝ ውህደት ነው?

፪ በዮርዳኖስ የሰው ልጆች የእዳ ደብዳቤ ለመፋቅ የተጠመቀው ማነው?

፫ ሰዎች ወደ ዮርዳኖስ ባሕር ይመጡ የነበሩት ለምንድን ነው?

፬ በዮርዳኖስ ‹‹መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ›› እያለ ሲያጠምቅ የነበረው የካህኑ አካርያስ ልጅ ማን ይባላል?

፭ በኢትዮጲያ ዮርዳኖስ የሚባል ወንዝ ታውቃላችሁን? ካወቃቹ የት ይገኛል?

ምዕራፍ ሰባት

መንግስተ ሰማያት

የምዕራፉ ዓላማ

ይህን ትምህርት ተምረው ሲጨርሱ

- ስለ መንግስተ ሰማያት ይረዳሉ።
- መንግስተ ሰማያት ያላትን ክብርና ልዕልና ያውቃሉ።

መንግስተ ሰማያት

መንግስተ ሰማያት ወይንም ኢየሩሳሌም ሰማያዊት በመባል ትታወቃለች ይህች ሥፍራ የተፈጠረችው በሥነፍጥረት ሥርዓት በእለተ እሑድ ነው። ይህችም ከሰባቱ ሰማያት አንዱ ስትሆን በዚህች በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወይንም መንግስተ ሰማያት ርሀብ፣ ማጣት፣ መጠማት፣ መታረዝ፣ የሌለበት ነው። ሁሉም በደስታ በፍቅር የሚኖሩባት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በአንድነት የሚመላለሱባት ምድር ነች። ይህች ምድር እጅግ ሰፊ ስትሆን ለብዙ ለጻድቃን ለቅዱሳን የተዘጋጀች ሥፍራ ነች። በበሮቿ እጅግ የሚያማምሩ እንዲሁም የተለያዩ ምሰሶዎች፣ ማረፊያዎች ያሉባት በእየሩሳሌም በመሀሏ ታቦት ዘዶር የተባለች የእመቤታችን ምሳሌ የሆነች ጽላት አለች።

መንግስተ ሰማያት ለመግባት ሁሉም ሰው ይሻል ከመሻቱም ባሻገር በምድር የሚያልፋቸው የሚያከናውናቸው ነገሮች አሉ አንደኛውና ዋነኛው ክፉውና ደጉን መለየት ነው። ክፉውን ጠልቶ ደጉን መፈጸም የሚችል ሁሉ መንግስተ ሰማያትን ይወርሳል ሁሉም ወደ መንግስተ ሰማያት ሲመጣ በንስሐ ይታጠባል ሕገ እግዚአብሔርንም ይጠብቃል ዘወትር ደግሞ በጸሎትና በጾም እንዲሁም በትሩፋት በስግደት በምጽዋት ይኖራል። ስለዚህ መንግስተ ሰማያት እጅግ ደስ የምታሰኝ ሥፍራ ነች በዚህም ሥፍራ ላይ ሁሉም በቅድስና ሕይወት የተመላለሱ ሕፃናት ለምሳሌ እንደነ ቅዱስ ቂርቆስ እንደነ ቅዱስ ኖብ እንደነ ቅዱስ ሚናስ እንዲሁም ደግሞ ከወጣቶቹ እንደነ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአረጋውያን እንደነ አባ እንጦስ እንደነ አባ መቃርስ ሐዋርያትም ሁሉ የታደሙበትና ወደፊትም የሚታደሙባት መልካም ሥፍራ ነች።

መልመጃ ሰባት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ

፩ መንግስተ ሰማያት በሌላ ስያሜዋ ምን ተብላ ትጠራለች?

፪ ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት የሚቻለው እንዴት ነው?

፫ የመንግስተ ሰማያት መልካም ስራዎች እነማን ናቸው?

፬ መንግስተ ሰማያት በምን ቀን ተፈጠረች?

ዋቤ መጻሕፍት

፩. የመጽሐፍ ቅዱስ መማሪያ በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ
፪. መሠረተ እምነት ለህጻናት በብጹእ አቡነ ጎርጎርዮስ

የሰንበት ት/ቤት አመራር እና መምህራን እንዲሁም ተማሪዎችና ወላጆች በመጽሐፉ ላይ ያላችሁን ማንኛውም አስተያየት እና ግብዓት በሚከተለው አድራሻ ላኩልን

office@eotc-gssu.org

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ሦስተኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጀ መምሪያ
የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ